# ምርጫ ለሰላም

sofiateshome@yahoo.com ሲቲና ከሀረር

ዘንድሮ በሚካሄደው 4ኛ ዙር አገራዊ ምርጫ የሥነ ምግባር ረቂቅ ደንብ ላይ በፖለቲካ ፓርቲዎች መሃከል እየተካሄደ ያለው ድርድር ወደ መገባደዱ ነው፡፡ በዚህ ድርድር ላይ ተሣታፊ የሆኑት ኢህአዴግ፣ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ፣ መላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኤዴፓ) እስከአሁን በተካሄደው ድርድር በአብዛኞዎቹ የደንቡ አንቀፆች ላይ ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ የጋራ ስምምነት ላይ ደርሰው ደንቡን ያፀድቃሉ ተብሎም ይጠበቃል፡፡

መድረክ እንደፓርቲዎች ጥምረት ሕጋዊ ዕውቅና ባይኖረውም፣ በስሩ የተሰባሰቡት ስምንት ፓርቲዎች እንደመድረክ እንዲሣተፉ ጠይቀው ተፈቅዶላቸው ነበር፡፡ በድርድሩ ላይ እያንዳንዱ ፓርቲ በአራት ተደራዳሪ ግለሰቦች የሚወከል ሆኖ ሣለ መድረክ በ16 /አስራ ስድስት/ ተደራዳሪ የመወከል እድልም ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ሁኔታ በኢሕአዴግና በሌሎች ተደራዳሪ ፓርቲዎች መድረክ ወይም በስሩ የተሰባሰቡት ስምንት ፓርቲዎች በድርድሩ ላይ እንዲሣተፉ የነበራቸውን ፍላጐት ያረጋግጣል፡፡

ሆኖም መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ በተባለው ቡድን ሥር የተሰባሰቡት ስምንት ፓርቲዎች ድርድሩ ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ ቢደረግላቸውም ከጅምሩ ጥለው መውጣታቸው ይታወቃል፡፡ በድርድሩ ላይ ለመሣተፍ ያቀረብኳቸው ቅድመ ሁኔታዎች ተቀባይነት አላገኙም ብሎ በራሱ ውሳኔ ነው ከድርድሩ ውጭ የሆነው፡፡ ቅድመ ሁኔታዎቹ፣ ተጨማሪ የድርድር አጀንዳዎች እና የድርድሩን አካሄድ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ለድርድሩ ያዘጋጀኋቸው ያላቸው አጀንዳዎቹ፣ ከኢህአዴግ በስተቀር ሦስቱን ተደራዳሪ ፓርቲዎች ስለማይመለከት፣ ከኢህአዴግ ጋር በተናጥል እንደራደር የሚል ነው፡፡ በግልፅ ባይናገሩትም "የተቀሩት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የእኛን /የመድረክን/ አቋም የሚቃወሙና የሚያጣጥሉ ናቸው…" በሚል እነርሱ የሚገኙበት ማንኛውም ውይይት፣ ላይ መሳተፍ እንደማይፈልግም ይታወቃል፡፡

ኢህአዴግ መድረክ ያቀረበውን ቅድመ ሁኔታ ያለተቀበለበትን ምክንያት በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይህም “ምርጫ የአንድ ወይም የተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጉዳይ ማይሆን፣ የሁሉም በምርጫው ላይ የሚሣተፉ ፓርቲዎች በመሆኑ ‘ከመድረክ’ ጋር በተናጥል መወያየት የለብኝም” የሚል ነው፡፡ ከድርድሩ ውጭ እንዲሆኑ የተጠየቁት ሦስቱ ፓርቲዎች የመድረክ ጥያቄ መብታቸውን ስለሚጋፋ እንዳማይቀበሉት ግልፅ ነው፡፡

መድረክ ቆየት ብሎ፣ አጀንዳዎቹን እንደያዘ “ወደ ድርድሩ እመለሣለሁ” ብሎ ሦስቱ ፓርቲዎች ድርድሩ ላይ ተስማምተው የሚያፀድቁበትን ጊዜ በአንድ ሣምንት እንዲያራዝሙ ዲፕሎማቶችን አማላጅ ላከ፡፡ ፓርቲዎቹ “ጥያቄው ተገቢ ባይሆንም፣ ለፖለቲካ ምህዳሩ መስፋት በማሰብ ተቀብለናዋል” ነበር ያሉት፡፡ በድርድር ሂደቱ የተስማሙባቸውን ጉዳዮች ወደ ኋላ ተመልሰው እንደማይመለከቱ፣ ያላዩዋቸው ጠቃሚ አዳዲስ ሐሣቦች ከመጡ ግን እንደሚቀበሏቸውም ነግረዋቸዋል፡፡ በድርድሩ ላይ እንዳይሳተፉ፣ መቼና እንዴት እንደተከለከሉ ባይታወቅም ሰሞኑን ለመሳተፍ በደብዳቤ ጠይቀን ምላሽ ተከልክለናል ብለዋል፡፡ ደብዳቤ መላኩ ይፋ ሲሆን ደግሞ ዘግይተው ስለደረሰን ነው ብለዋል፡፡ አሁንም ግን የለየለት አቋም መያዝ አለመያዛቸው በግልጽ አይታወቅም፡፡

ይህን በዚህ ትተን መድረክ ሊደራደርባቸው ያላቸውን አጀንዳዎች በራሳቸው ለድርድር መቅረብ የመቻላቸውን ጉዳይም እንመልከት፡፡

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር የወ/ሪት ብርቱካን እስርና የምርጫ አስፈፃሚው ገለልተኝነት፣ የሚሉትን ሁለት አጀንዳዎች እንደምሣሌ እንውሰድ፡፡ እነዚህን እንደናሙና የወሰድናቸውን ሁለት ጉዳዮች አንድ በአንድ እንመልከት፡፡

እርግጥ ነው፣ ከመድረኩ ስብስቦች አንዱ የሆነው አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሣ በእስር ላይ ናቸው፡፡ ይህን የመድረክ

አጀንዳ ተገቢነት ወይም ተገቢ አለመሆን ለመረዳት ጉደዩን “ከፖለቲካ እስረኛ” ምንነት እና በተለይ ከወ/ሪት ብርቱካን እስር  አኳያ መመልከት ይሻል፡፡

የፖለቲካ እሰረኛ አንድ የመንግስት ሥርአት ከሚያራምደው አመለካከት የሚቃረን የተለየ አመለካከት አቋም ስለያዘ ወይም በይፋ ስለገለፀ ብቻ፣ ይህ እንደጥፋት ተቆጥሮ የታሠረ ማለት አይደለም፡፡ እነዚህ መብቶች በሕገ መንግስት ላይ ሰፍረው በተከበሩበት የፖለቲካ ስርዓት፣ የፖለቲካ እስረኛ የሚባል ነገር አይኖርም፡፡ ወንጀል ፈፅሞ በእስር ላይ የምትገኝን ግለሰብ፣ በፖለቲካ እንደታሰረች አድርጎ ማራገብ በራሱ ሌላ ጥፋት ነው፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ግለሰቦች ያመኑብትን አመለካከት የመያዝ፣ በአመለካከት የመደራጀት፣ አመለካከትን የማራመድ፣ ለፖለቲካ ሥልጣን መፎካከር መብትና ነፃነት የተከበረ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ መደንገግ ብቻ ሣይሆን መከበሩ በተግባር ተረጋግጧል፡፡ የወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሣን ጨምሮ የተለየ አቋም ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች የተመሰረቱትና በይፋ አቋማቸውን የሚያራምዱት በዚሁ መሰረት ነው፡፡

የ97ን የምርጫ ሂደት አቋምን፤ ለሕዝብ የማስተዋወቅ በፖለቲካ ፖርቲዎች መካከል የተደረገ ውይይት የምረጡኝ ቅስቀሣ የድምጽ አሰጣጡን ሂደት ያስታወሰ፣ እነ ወ/ሪት ብርትኳንና ሌሎቹም ምን ያህል የአመለካከት ነፃነታቸው እንደተከበረና ለስልጣን የመፎካከር መብታቸውን እንደተጠቀሙ ያስታውሣል፡፡ ይህን ሕገ መንግስታዊ ሠላማዊ አካሄድ ገፍቶ፣ ስልጣን ለመያዝ ማሴር፣ ማስፈፀምና መፈፀም ግን ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካኛ መሆን፣ በሕግ የተከለከለ የወንጀል ድርጊት የመፈፀም፣ የማስፈፀም መብት አያስገኝም፡፡ ወንጀል የፈፀመ ፖለቲከኛም ቢሆን በወንጀሉ ይጠየቃል፡፡ ወ/ት ብርትኳን የፖለቲካ እስረኛ ሳይሆኑ ሕግ የተላለፉ ተራ ወንጀለኛ የሚሆኑት  ለዚህ ነው፡፡  የሕግ እሰረኛን ሕግ ከሚፈቅደው ውጭ ከእስር የማስለቀቅ መብት ወይም ስልጣን ያለው አካል የለም፡፡

ወደ ወ/ሪት ብርቱካን መታሰር ስንመለስ፣ እንዲታሠሩ ያደርጋቸው የቅጣት ውሳኔ የተላለፈው 2001 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ዳግም ተይዘው ማረሚያ ቤት የገቡ ጊዜ አለመሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ምርጫ 97ትን ተከትሎ በተነሣው እና በመቶዎች ለሚቆጠሩ ሠላማዊ ዜጐችና ሕግ በማስከበር ተግባር ላይ ተሠማርተው

የነበሩ የፀጥታ ኃይሎች ሕይወት መጥፋት፣ በሚሊዮን ብር የሚቆጠር የመንግስት፣ የሕዝብና ያግለሰቦች ንብረት ውድመት ምክንያት በሆነው፣ በአዲስ አበባና ሌሎች ጥቂት የአገሪቱ ትላልቅ ከተሞች በተነሣው ሁከት ጠንሳሽነት፣ ክስ ተመስርቶባቸው አንድ አመት ከመንፈቅ ያህል በፈጀ የፍርድ ሂደት፣ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው፣ ሐምሌ 1999 ዓ/ም ባሳለፈው የቅጣት ውሣኔ ነው፡፡

ከምርጫ 97 በኋላ፣ እነወ/ሪት ብርቱካንን ለክስ ያበቃው ሁከት መቀስቀሱ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ ይህን ያወቅነው በስሚ ስሚ ወይም ከመገናኛ ብዙሃን ዜና አይደለም፡፡ ሲፈፀም አይተነዋል፡፡ ሁከቱ ደግሞ፣ ድንገት እንደመብረቅ የወረደ ሳይሆን ጠንሣሽ፣ አስፈፃሚና ፈፃሚ አለው፡፡ እንግዲህ ወ/ት ብርቱኳንና አባሪዎቻቸው ይህን ሁከት፣ ሕገ መንግሥታዊውን ሥርአት በኃይል ለመናድ የሁከቱን ሴራ በመጠንሰስና፣ በማስፈፀም ወንጀል ተጠርጥረው፣ ከሣሽ አቃቤ ሕግ ያቀረበው ማስረጃ ጥፋተኛ መሆናቸውን ስላረጋገጠ፣ ተከሳሽም ጥፋተኛ አለመሆናቸውን መከላከል ስላልቻሉ፣ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት፣ በአገሪቱ የወንጀል ሕግ መሠረት የእድሜ ልክ የቅጣት ውሣኔ አሣልፎባቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ወ/ት ብርትኳንን ጨምሮ በተመሳሳይ ጥፋት ተከሰው ቅጣት የተወሰነባቸው ታራሚዎች፣ ጥፋተኛ መሆናቸውን አምነው፣ በድርጊታቸው መፀፀታቸውን ገልፀው ፣ ሕገ መንግሥቱን አክብረውና አስከብረው ለመኖር ቃል ገብተው ይቅርታ እንዲደረግላቸው ፊርማቸውን ባሣረፉበት ደብዳቤ ጠየቁ፡፡ በዚሁ መሠረት፣ ፍርደኞቹ ባቀረቡት ከጥፋታቸው ይታረማሉ በሚል እምነት፣ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ይቅርታ ተደርጎላቸው ከእስር መውጣታቸውን አገር የሚያውቀው እውነት ነው፡፡ ይቅርታው የተሰጠው፣ የመንግሥት ስልጣን ላይ ባሉ ግለሰቦች የሕሊና ፍርድ ሣይሆን፣ ወንጀለኞች የሚቀጡበትን የሕግ አላማ ተንተርሶ በተደነገገ የይቅርታ ሕግ መሠረት ነው - ቅጣቱም፣ ይቅርታውም በሕግ የተሰጠ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ከአንድ ዓመት በኋላ፣ " ወ/ሪት ብርቱካን ከእስር የወጣሁት ይቅርታ ጠይቄ በይቅርታ ሕግ መሠረት አይደለም" ብለው በይፋ ካዱ፡፡ ይቅርታ ከመጠየቅ፣ ከይቅርታ ሕጉ ውጭ ቅጣት የተወሰነበት ታራሚ፣ የቅጣት ጊዜውን ሳይጨርስ ከእስር የሚወጣበት ምንም መንገድ የለም፡፡ ማንም ይህን የማድረግ ሥልጣን የለውም፡፡ ወ/ሪት ብርቱካን ይቅርታ አልጠየኩም ካሉ ከእስር

የወጡት፣ አምልጠው እንዳልሆነ ስለሚታወቅ፣ ይቅርታው የተሰጣቸው ይቅርታውን ሳይጠይቁ በስህተት ነው ማለት ይሆናል፡፡ ይህ ሲታወቅ ቅጣቱ ተፈፃሚ መሆኑ የግድ ነው፡፡

በመሆኑም ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን እስር የሚመለከተው የመድረክ አጀንዳ ለድርድር የማይቀርብ የሕግ የበላይነት ጥያቄ ነው፡፡ ኢሕአዴግ ራሱ፣ በሕግ ሥር ያለና አገሪቱን በሕግ እንዲያስተዳድር በሕዝብ ውክልና ስልጣን የተሰጠው አካል እንጂ፣ የሕግ ጉዳይን በመደራደር የመለወጥ ስልጣን ያለው አካል አይደለም፡፡ ይህን አድርጎ ቢገኝ በሕግ ይጠየቃል፡፡

ሌላው መድረክ ለድርድር ያዘጋጀው አጀንዳ የምርጫ አስፈፃሚ አካል ገለልተኝነትን የሚመለከት ነው፡፡ የምርጫ ጉዳይ የሚመለከተው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን በመሆኑ ስለዚህ ተቋም ገለልተኝነት ለመደራደር የቀረበ ጥያቄ ከመሆን አይዘልም፡፡

ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በሕገመንግስቱ መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ባፀደቀው ሕግ የተቋቋመ ተቋም ነው፡፡ ቦርዱ ተግባራቱን የሚያከናውነው፣ የቦርዱ ሰብሳቢና የቦርድ አባላቱ የሚሰየሙት በዚሁ ሕግ መሠረት ብቻ ነው፡፡

ያለፉትን 3 ምርጫዎች የተካሄደባቸው የምርጫ ሕግ ተሻሽሎ ሰኔ 1999 ዓ.ም ላይ መጽደቁ ይታወቃል፡፡ በዚህ የምርጫ ሕግ መሠረት የምርጫ ቦርድ አባላት የሚሾሙት በጠቅላይ ሚኒስትሩ እጩዎችን አቅርበው በም/ቤቱ መቀመጫ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች የዕጩዎቹን ገለልተኝነት ካረጋገጡ በኋላ በአብላጫ ድምፅ ሹመቱን ሲያፀድቁ ነው፡፡

ስለዚህ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንደ ተቋም እንዲሁም የቦርዱ አባላት ገለልተኝነት ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች የሕግ ጉዳይ ናቸው፡፡ ገለልተኛ አለመሆናቸውን የሚያረጋግጥ ተጨባጭ ማስረጃ ሲኖር፣ ጉዳዩ አግባብ ባለው ህግ ነው የሚታየው፡፡ ማንም በዚህ አጀንዳ ላይ በመደራደር ህጉ ከሚያዘው ውጪ የመስማማት ስልጣን የለውም፡፡ የህግ የበላይነት ለድርድር ስለማይቀርብ፡፡

በመድረኩ ሥር ከተሰባሰቡት የፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱና የመድረኩ መስራች የሆነው የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች ኃይሎች ሕብረት ከፍተኛ አመራርና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆኑት የተከበሩ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ የምርጫ ቦርድ አባላትን ምክር ቤቱ ባፀደቀበት እለት ለቦርድ አባልነት የተቀመጠውን “ለሕገመንግሥቱ ታማኝ የሆኑ” የሚል መስፈርት ገለልተኝነታቸውን አጠራጣሪ ያደርገዋል፣ የሚል አቋማቸውን ም/ቤት ውስጥ ገልፀው ነበር፡፡ ምናልባት መድረክ የቦርዱን የገለልተኝነት ጉዳይ ያነሣው፣ የፕሮፌሰር በየነ አቋም ተጋብቶበት ይሆን?

እንደ ፕሮፌሰር በየነ እምነት የምርጫ ቦርድ አባላት ገለልተኛና ኃላፊነታቸውን በተገቢው መንገድ የሚወጡ መሆናቸው የሚረጋገጠው፣ ሕገ መንግሥቱን ያልተቀበሉ ሲሆኑ ነው፡፡ ፕሮፌሰሩ ይህን የተናገሩበት ምክር ቤት የተቋቋመው፣ እርሳቸው የሚመሩት ፓርቲ የተመሠረተው፣ ለምክር ቤት አባለነት የበቁት በሕገ መንግሥቱ መሠረት መሆኑን መዘንጋታቸው ያስገርማል፡፡

በአጠቃላይ መድረክ በመጪው ምርጫ ረቂቅ የስነምግባር ደንብ ድርድር ላይ ለመሣተፍ ያስቀመጠው ቅድመ ሁኔታ፣ ኢ.-ዴሞክራሲ የሕግ የበላይነትን የሚፃረር ነው፡፡ በመሆኑም፣ ብዙዎች መድረክ ይህን በድርድር ሊታይ የማይችል አጀንዳ ያቀረበው፣ በድርድሩ ላይ ላለመሳተፍ ሰበብ ይሁነኝ በሚልና እስካሁን በግልጽ ያልታየ ስውር አጀንዳ ኖሮት፣ ይህንኑ ማስፈፀሚያ ክፍተት ፍለጋ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አድሮባቸዋል፡፡ ስውር አላማው “ያላፀደኩት ደንብ አይገዛኝም” በሚል እምነት ምርጫውን” የዶ/ር ነገደ ጎበዜ አይነት መሬት አንቀጥቅጥ አመጽ፣ ማስፈፀም እንዳይሆን ግን ሠላማዊ ዜጐች ሁሉ እንመኛለን፡፡ ሰላም!!